



Aberash Berta
አበራሽ በርታ



Tsegaye Gebre-Medhen
ጸጋዬ ገብረመድህን

ደብተራው



ይስሐቅ ደብረፅዮን
Yishak DebreTsion



Assefa Maru
አሰፋ ማሩ

በወያነ መሪዎች የተገደሉ ኢትዮጵያውያን ሰማዕታት

# አቶ ገብሩ አስራት የወያነን ድርጅት ትተው የድል

# አጥቢያ አርበኛ በመሆን ተቃዋሚ ጎራ ሊገቡ ነው

ከገታቸው ጋረደው

የዓረና ትግራይ ድርጅት መሪ አቶ ገብሩ አስራት በአሜሪካ ዋሽንግተን ከተማ ነሀሴ 20/ 2008 ለከተማው ነዋሪዎች ንግግር አደረጉ። አቶ ገብሩ አስራት ከሁለት ሳምንት በፊት በራዲዮ ከአዲስ አበባ ቃለ መጠይቅ እንዳደረጉ ሲታወስ አሁን ባህር አቋርጠው ወደ አመሪካ የመጡት መለስ ዘናዊ ለኢትዮጵያ ህዝብ ያወጣለትን አዲስ ህግ ለአድማጮቻቸው ለማብራራት ነበር። ስምንት ገጾች በፈጀው ንግግራቸው ከምርጫ 97 በኋላ የፖለቲካ ማህደሩን የሚያጠቡ ተጨማሪ አዋጆችንም አርቅቋል አጽድቋል፡ ኬነዚህ አዋጆች መካከል የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና አዋጅ የፕረስ አዋጅና የእርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ወይም የሲቢል ማህበር ሰብ አዋጅ ተጠቃሾች ናቸው። የጸደቀው የፓርቲ ምዝገባ አዋጅ ዋና ይዘት ፓርቲዎች ጠንካራ የፋይናንስ ምንጭ ኖሯቸው ተፎካካሪ እንዳይሆኑ ለማድረግ ያለመ ነው፡ በመሆኑም ፓርቲዎች ከውጭ መንግስታት እርዳታ ሰጪዎችና የውጭ ፓስፖርት ካላቸው ትውልድ ኢትዮጵያውያን ገንዘብ እንዳያሰባስቡ የሚከለክል አንቀጽ ሰፍሯል፡ እነዚህ እርምጃዎች እየተወሰዱ ያሉ የአገር ሉኡላዊነት ለማስከበር ነው የሚል ሽፋ ንቢሰጥም እውነታው ግን የፓርቲዎ ችን እንቅስቃሴ ለማሽመድመድ የተቀየሰ መሆናችውን እንዲሁም ለሎች የኤክኖሚ ህጎች መዘጋጃታቸውን ሲገልጹ፣ ይህ አካሄድ አሁን ያሉትየኤኮኖሚ ንድፈ ሀሳቦችን መሰረት ያደረገ ሳይሆን ስልጣን በመኖፖል ለመቆጣተር ይበጃል ተብሎ የተነደፈ ነው ይላሉ አቶ ገብሩ።

አቶ ገብሩአዲስ የወጣ ህግ ነው ብለው የሚነግሩን ህጎች አሳቸው እንድሚሉት አዲስ አይደለም፣ የወያነ መስራቾች ደበቢት በረሃ እንደገቡ ያዘጋጁት ህግ ሲሆን ሁሉንም በአንድ ጊዜ ለህዝብ መግለጽ ህዝቡን የሚይስደነግጥ ከመሆኑ ለላ ህዝቡን ለአመጽ ይገፋፋል በሚል ፍራቻ በምስጢር ይዘውት ቆይተዋል፣ ነጻነት የጎደለውና በአንድ ፓርቲ የበላይነት የሚመራው የአገራችን ፖለቲካ ጉዳዮችና በአገራዊ ጥቅም ዙሪያም አጅግ የጎዳን ይገኛል፣ ከነዚህ ችግሮች አንዱ ለአመታት በአንጥልጥል ላይ ያለው የኢትዮ የኤረትራ ግንኙነት ነው፣ ከሻቢያ ጋር ያለን ግንጁነት አሁንም መቋጫ አልተበጀለትም፣ የአልጀርስ ስምምነት ተደርጎ ይድንበር ኮሚሽኑ ያኣገራችንን ሉአኡላዊ ግዛት ለሻቢያ አሳልፎ ከሰጠ በኋላም ይሁን ከዘያ በፊት የአልጀርሱ ስምምነt ፈርሳል ቢሉም፣ የአልጀርሱ ስምምነት የአገራችንን ሉኡላዊ ግዛት ለሻቢያ አስልፎ ሰጠ ያሉት ትክክል አይደለም። ያለአንዳች ምክንያት የባድማና የአካባቢው ወሰኖች አልጀርስ ከተማ ውይይት እንዲደረግባቸው ሀሳብ ያቀረበው ማነው? አንባ ገነኑ መለስ ዘናዊና እናንተ መሆናችሁን ዘነጋችሁት? በ 1983 ለንደን ከተማ በተደረገው ስብሰባ ከናንተ ከወያነዎች ጋር ተሰብስበው ድምጻቸውን የሰጡት ኤረትራውያን

ሰብስቦ ያመጠው ማነው? አስራት ገብሩና ሰዬ አብርሃ መሆናችሁን ዛሬ ለመካድ ከፈለጋችሁ የምትጎዱት እራሳችሁን እንጂ የኢትዮጵያን ህዝብ አይደለም ስለዚህ የአገር ክህደት ስራ ለእናንተ ለወያነዎች በዝርዝር መግልጽ ለቀባሪው አረዱት እንደሚባለው ቢሆንም፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ከጀርባው የተሰራበትን ሴራና ተንኮል እንዲያውቀው ማድረግ አስፈላጊ ስleሆነ እንዴት እንደተጀመረና እንድተፈጸመ በጥቂቱ አንተንትን። በ 1983 መለስና የወያኔ፣የሻቢያ ከፍተኛ መሪዎች፣ የአነግ ተወካይ በተገኘበት የኢትዮጵያው ተወካይ ባልነበረበት ለንደን ከተማ በተደረገው ስብሰባ የአሰብ እድል ምን እንደሆነ በተወሳበት ጊዜ የአሜሪካ መንግስት ተወካይ Herrmann Kochen ባቀረበው ሀሳብ፣ አሰብ የኤረትራ ግዛት ነው ካላችሁ ኢትዮጵያ ያለወደብ መቅረት ስልማይገባት አሰብ የኢትዮጵይ ግዛት መሆን ይገባዋል በማለት ቢናገር፣ መለስ ጠረጴዛውን በእጁ እየደበደበ ይህ መሆን አየገባውም ብሎ ስልጮኽ ሁሉም የሱን ሀሳብ በመቀበል መስማማታቸውን በጭብጨባ ስታረጋግጡ ጭብጫቢው ብዙ መስሎ እንዲታይ በርከት ያሉ ኤሬትርውያን እንደ ኢትዮጵያውያን መስለው፡ቆመው፡እንደነበር፡በወቅቱ፡በስፍራው፡የነበሩ፡ተካፋዮች ተናግረዋል ከዚህ በኋላ ኢሳይያስና መለስ ኢትዮጵያን፡ሲከፋፈሉ፣መለስ ኤረትራ ከቅኝ ገዢዋ ከኢትጵያ እንድትገነጠል ለተባበሩት መንግስታት ዋና ጸሀፊ ማመልከቻ ከመጻፍ አልፎ፣ መለስ የቅኝ አገር መሪ በመሆን አስመራ ሄዶ በግንጠላው ስነ ስርአት ህያው ምስክር ሆነ፣ ከግንጠላው በኋላ መለስና ኢሳይያስ በነበራቸው አፍላ ፍቅር ኤሬትራ ለሰባት አመታት ኢትዮጵያ የጋራችን ኤሬትራ የግላችን በማለት ሲዘርፉን ሲመዘብሩን ከቆዩ በኋላ ሁለቱም አገሮች የየራሳቸውን ገንዘብ ሲያሳትሙ፣ ኢሳይያስ የዘረፈን ሳያንሰው የኢትዮጵያ ብርና የኤሬትራ ናቅፋ ምንዛሪ አንድ ለአንድ መሆን አለበት በማለት ደንፍቶ ከመጮህ አልፎ አንድ ጥይት ሳይተኩስ የኢትዮጵያን ግዛት ባድማን በቁጥጥሩ ስር አዋለ፣ መለስ ኤሬትራ አትወጋንም በማለት ወሰኑን ያለ ጠባቂ ስለተወው፣ የወያነ ጀሌ ወታደሮች ሻቢያን ለመቋቋም ስለአልቻሉ የሻቢያወታደሮች ለረጅም ጊዜ፡ኢትዮጵያ ውስጥ ሲቆዩ በመጨረሻ መለስ የሚያደርገው ነገር ስለአጣ የበታተናችሀውን የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ሰብስቦ ስለዛእዘመታቸው፡ወደ ተመደቢበት ጦር ሰፈር ሄዱ።

ውድ አንባቢዎች፣ ከዚህ በታች ያሉትን ጥቂት መስመሮች፣ መለስ ዜናዊና ገብሩ አስራት ሰዬ አብርሃና ለሎች የወያኔ የበላይ ሹማምንቶች በዚህ ጦርነት በኢትዮጵያ ወታደሮች ላይ የሰሩትን ግፍና በደል በአንክሮት እንድ ታነቡት አደራ እንላለን።ወታደሮቻችን የተመደበላችውን ቦታ ከያዙ በኋላ ባድሜን አስመልሰው የአሰብን ወደብ ለመያዝ ሰላሳ ሰባት ሊሎሜትር ሲቀራችሀው መለስ ከእንቅልፉ ተነስቶ ወታደሩ አሰብን እንዳይዝ ወድኋላ እንዲያፈገፍግ ስለአዘዘ ተዋጊው ጦር ፊቱን አዙሮ ሲመለስ የሽቢያ ወታደሮች ከኋላው፡መጥተው ስለተኮሱበት በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ወታደሮች በከንቱ አለቁ፣ በባድማ ጦርነት አስከሰማኒያ ሹህ ህዝብ እንዳለቀ ታውቋል። ይህ ሁሉ ህዝብ ያለቀው በመለስና በወያነ

መሪዎች ስህተት ሲሆን እነዚህ ወንጀለኞች ጦር ፍርድ ቤት ቀርበው መቀጣት ሲገባቸው፣ መለስ አሁንም በአንባ ገንነት ኢትዮጵያን ሲገዛ፣ እነገብሩ አስራት ካለፈው ስህተታቸው ባለመማር አሁንም እንምራችሁ እያሉ ያፈዙብናል። የባድማ ጦርነት ከተፈጸመ በኋላ የትግራይ ተዋጊዎች መሳሪያቸውን እንዳነገቱ እንደድል አድራጊ ጀግኖች ወሮ ወሸባዬ እየተዘነፈላቸው በክበሮና በንቢልታ ታጅበው በመኪና ወደሰፈራችሀው ሲመለሱ፣ የኢትዮጵያ ወታደሮች መሳሪያቸውን አስረክበው በእግር ጉዞ ወደ መጡበት ክልል እንዲመለሱ ስለተገደዱ ብዙዎች በድካምና በበሽታ እቤታ ቸው ሊደርሱ አልቻሉም፣ እስከዛሬ የት እንደደረሱ አልታወቀም፣ ከዚህ ሌላ በጦርነቱ ለተዋጉ ጀግኖች ሽልማት እንዲሰጥ ስለታዘዘ ከሶስት ሚሊዮን የትግራይ ህዝብ ሰላሳ ሰባት ጀግኖች ሲሸለሙ ከሰማኒያ ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን ሶስት ጀግና ብቻ ተሸለመ፣ በጦርነቱ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወታደሮች ሲሞቱ፣ ሻቢዎች የወታደሮቻቸውን አስከረኖች አንድም ሳይተዉ በመቅበር ወይም በመኪና በመጫን ሲወስዱ የኢትዮጵያ ወታደሮች አስከረን እየተመረጠ ወደጎን ሲሰበሰብ የትግራይ ተወላጆች አስከረን በየዘመዱ ተከፋፍሎ ተቀበረ፣ የኢትዮጵያ ወታደሮች አስከሬን በተጣለበት ስፍራ በስብሶ ሽታው አካባቢውን ስለበከለው የተባበሩትመንግስታት ድርጅት ዋና ጸሀፊ ኮፊ አናን ይህንን አሳፋሪ ኢ/ሰብአዊ ድርጊት ስለሰሙ፣ በጣም በመቆጣት አንድ ወታደር ለአገሩና ለመብቱ በጦርነቱ ሲሞት በክብር ተቀብሮ መታሰቦያ ሊሰራለት ሲገባ፣ የአውሬ ምግብ ማድረግ አሳፋሪ ነውበማለት ስለወቀሱ፣ የተበታተነውን አስከረን በስፍራው የነበሩ ባለስል ጣኖች አስከረኑን በቡልዶዘር ሰብስበው በአሳት ማቃጠላቸውን እለታዊ የአገ ራችን ጋዘጣ በሰፊው አውጥቶታል። መለስና ወያኔዎች ለኢትዮጵያ ወታደሮች የከፈሉት ምስጋና ይህ በመሆኑ እጅግ ያሳዝናል።

ኢሳይያስ አፈወርቂ በባድማ ጦርነት በመሸንፉ መለስ በጣም ሲያዝን፣ አንድ ዘዴ ፈልጎ ባድማን ለኢሳይያስ ለመስጠት ስለፈለገ ጉዳዩ በፍርድ እንዲወሰን ሲያሳስብ፣ የአልጀሪያ መንግስት የበኩሉን እርዳታ በማድረግ ፍርድ ቤቱ ሆላንድ ውስጥ እንዲደረግ ሲወስን መለስ ማንም ሳይጠይቀው ሳያስገድደው ፍርድ በቱ የወሰነውን ማናቸገውንም ውሳኔ ተቀብዬ በተግባር ለማዋል ዝግጁ ነኝ ሲል ቃሉን ሰጠ፣ ፍርድ ቤቱ ስራውን እንደ ጀመረ፣ ፍርድ ቤቱ ላቀረበው ጥያቄ የመለስ ጠብቃ አጥጋቢ መልስ የማይመልስ ከምሆኒም በላይ አጼ ምንሊክ ከጣሊያን መንግስት ጋር በ 1902 አንድ ስምመነት ተፈራርመዋል የተሳለም ካርታ ይገኛል ቢልም የንጉስ ነገስቱን ወይም የወኪላቸውን ፊርማ ለማቅረብ አልቻለም፣ ይሀንን የተመለከቱ ኢትዮጵያውያን ህግ አዋቂዎች ያለ ክፍያ ኢትዮጵያን ለመወከል እንፈልጋለን ብለው ቢጠይቁ መለስ አሻፈረኝ በማለት በሚሊዮን የሚቆጠር ብር ለፈረንጆች ከፍሎ ተረታ። መለስ ክሱን ያቀረበው ለይምሰ ል እንጂ ለኢትዮጵያ ህዝብ በማሰብ አይደለም፣ ያሱ ፍላጎት ባድሜን ለኤሬ ትራ ለመስጠት ስለነበር ይህ ለጊዘው ተሳካለት። አቶ ገብሩ ባደረጉት ንግግር፣ የአልጀርሱ ስምምነት ተደርጎ የድንበሩ ኮሚሽን የአገራችንን

ሉኡላዊ ግዛት ለሻቢያ አሳልፎ ሰጠ ይላሉ፣ ይህ አባባል ትክክል አይደለም፣ ፍርድ ቤቱ ውሳነ በሰጠበት ቀን ፍርድ ቤቱ ውስጥ ለመግባት ባንችልም ብዙዎቻችን በአካባቢው ተገኝተን ውሳነውን አዳምጠናል፣የወያኔ የውጭ ጊዳይ ሚኒስትር ስዩም መስፍን ከፍርድ በቱ እንደ ህጻን ልጅ እየቦረቀ አሸነፍን ከምንፈልገው የበለጠ አገኘን እያለ ሲወጣ አበደ ብለን ስቀንበታል፣ በዚያኑ ቀን መቀሌ ገብቶ በውሸት አሸነፍን በማለት ለትግራይ ህዝብ ስለነገረ. ህዝቡ እውነት መስሎት ሶስት ቀናት ከበሮውን እደለቀ እንቢልታውን እየነፋ ሲጨፍር ከረመ፣ ከሶስት ቀናት በኋላ ውሸት መሆኒ ተገለጸ፣ ለአንተ ነው የቆምነው የምትሉትን የራሳችሁን ህዝብ እንደህጻን ልጅ ማታለል አያሳፍራቸሁም? መለስ ሳይጠየቅ ሳይለመን የፍርድ ቤቱን ውሳነ ያለ ይግባኝ ተቀብዬ በተግባር አውላለሁ ያለውን ቃል ፈርድ ቤቱ በማስታወስ በተግባር እንዲያውል መለስ ቢጠየቅ አሻፈረኝ ስላለ ብሁለቱ አገር መካከል ጸጥታውን ይጠብቁ የነበሩት የተባበሩት መንግስታትት ወታደሮች በሙሊ አካባቢውን ለቀው ስለሄዱ፣ ኢሳይያስ አፈወርቂ የፍርድ በቱ ውሳኔና የወሰኑ አቀማመጥ የተሳለበት ካርታ ግልባጭ ከተሰጠኝ በተጨማሪ የምፈልገው ነገር የለም በማለት እጁን ሰብስቦ ሲቀመጥ ከሰላሳና አርባ አመታትት ብኋላ በእጁ ያለውን መረጃ በማቅረብ ልጆቻችንን መጠየቁ አይቀሬ ነው።ለዚህ ይቅርታ የማይገባው ስህተት ተጠያቂው መለስ ዜናዊ ብቻአይደለም፣ እናንተም ገብሩ አስራትና ተባባሪዎች ተጠያቂዎች ናችሁ፣ ባድሜንና የአሰብን ወደብ በተመለከተ መለስ ዜናዊ ስልጣኑን ለማራዘም ኤረትራን ለመውጋት እየተዘጋጀ ሲሆን የአሜሪካ መንግስት ሃሳ ቡን በመደገፍ ፕሬዜዳንት ቡሽ ስልጣናቸውን ከመልቀቃቸው በፊት በርከ ትያለ መሳሪያ እንደሚልኩ ታውቋል ባለፈው ትርጉም ለሌለው የመለስ ጦርነት ህዝባቸን በከንቱ ህይወቱን ሰውቷል፣ ኬንግዲህ ወዲህ አሰብን በሰላ ም ከኤሬትራ መንግስት ጋር ተነጋግሮ ለማስመለስ ስለሚቻል በኢትዮጵያ ችን ኢትዮጵያዊ መንግስት እስኪመሰረት ድረስ መጠበቅ አስፈላጊ ነው። አኢሳይያስ አፈወርቂ ኤረትራ የምታፈራውን ሰብልና ሸቀጥ ለማስገባትና ለማስወጣት፣ የምጽዋ ወደብ በቂ ስልሆነ አሰበን ከኢትዮጵያ ነጥቆ የግመል መፈንጫ ቢያደርገው ከጉዳት በስተቀር ጥቅም ስለማያገኝ በሰላም ለኢትዮጵያ ቢመልስ ከፍተኛ ጥቅም ያገኛል፣ ኢሳይያስ በስሜት ተነሳስቶ አሬትራን ከኢትዮጵያ መገንጠሉ ጎዳው እንጂ አልጠቀመውም. ስህተተን ማረም. የመሻሻል ምልክት ስልሆነ አብረን በሰላም ብንኖር ተጠቃሚው ሁላችንም ስልሆን እናስበበት።

እናንተ ወያነዎች በስልጣን ላይ በነበራችሁበት ወቅት የኢትዮጵያን ህዝብ በመናቅ በትእቢት በመሳሪያ ሀይል መብቱን ገፉችሁ፡እንድቅኝ፡ተገዢ ህዝብ ስትገዙት፣ ይህ አልበቃ ብሏችሁ ህዝቡ በረሀብ ከነልጆቹ እንዲሞት ያደረጋችሁት ሳያንስ ባለፉት አስራ ሰባት አመተት ከሞላ ኢትዮጵያ እየዘ ረፋችሁ በየባንኩ የደበቃችሁተን ገንዘብ ወደአገሪቱ መልሳችሁ፡ለህዝቡ በማ ደል ፈንታ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት እንዲረዳ ጠዋትና ማታ ምጽ ዋእት ትለምናላችሁ፣ ንጉስ ሀይለ ስላሴ ከአልጋ ውራሽነታቸው ጀምሮ

ከኢትዮጵያ ህዝብ እየነጠቁ በስዊስ ባንክ ያጠራቀሙት ገንዘብ የባእዳን ሀብት ሆኖ እንደቀረው ሁሉ እናንተም በመስገብገብ የዘረፋችሁት ገንዘብ የ ባእዳን መጠቀሚያ ሆኖ እንደ ሚቀር የታወቀ ነው።
አቶ ገብሩ አስራት በማውቅ ይሁን ባለማውቅ በገጽ 7 የተናዝገሩት መንግስት በመጀመሪያ ላይ ሁለቱ አገሮች ድንበር አካባቢ ምንም አይነት ችግር የለም፣ ቢልም ቀስ በቀስ ሀቁ ሲጋለጥ የተምታቱ መግለጫዎች ለመስጥት ተገዷል፣ ኢኢሃደግ ካለው የአገር ጥቅምና ሉኡላዊነት የመቆጣጠር ችግር ስንመለከተው ይህም ሌላው የሚያሳስበን ጉዳይ ሆኗል፣ ይህ ጉዳይ ህዝቡ አውቆት ካልተካሀደ አሁንም የሚፈጠረው ጦስ ቀላል አይሆንም ጊዳዩ የገንደር ወይም የአርማጮሆ አካባቡ ሳይሆን የመላ ዜጎች ጉዳይ ነው፣ በመሆኑም እንዲህ ተዳፍኖ ማለቅ የሌለበት ጉዳይ ነው ይላሉ፡ አሳችው ይህንን ለማስመሰል ውይንም እኛን ኢትዮጵያንን ለማዘናጋት ያሉት ቢሆንም፣ ችግሩ የኢትዮጵያና የሱዳን ሳይሆን የኢትዮጵያና የትግራይ ህዘብ ነው፣ መለስና እናንት ግብር አበሮችና እንዲሁም አረጋዊ በርሄ ደበቢት በረሃ በነበራችሁት ወቅት ከጎንደርና ከወሎ ግዛት ሰፊ ለም መረት ቆርጣችሁ በትግራይ ክልል ስለአካለላችሁ፣ በ 1983 ኢትዮጵያን በወረራችሁበት ማግስት፣ የሁለቱን አገር ህዝብ ስደተኞች በማድረግ አገሪቱ የምታፈራውን ሀብት በመንጠቅ የትግራይን ሰደተኞች ባለ፡ንብረት ስላደረጋ ችሁት ከጎንደርና ከወሎ የተባረረው ህዝብ እስከዛሬ ሰደተኛ ሆኖ ይንከራተ ታል፣ ይህ አግባብ ነው ትላላችሁ? አናንት የትግራይን ክልል ሉኡላዊነት ስታስከብሩ፣ የጎንደርንና የወሎን ሉኡላዊነት ለመግፈፍ የተለየ መብት አላችሁ? ይህ በንቀትና በማን አለበኝነት የሚደረግ ግፍ ቀኑን ጠብቆ ሲፈነዳ ምን ትላላችሁ? ለአገራችን ችግር መፍትሄ ለማግኘት ተቃዋሚዎች በሙሉ እናንተም ጭምር ስትሰበሰቡ፣ የጎንደርንና የወሎን ሉኡላዊነት ካላከ በራችሁ በስብሰባው ልትካፈሊ አትችሉም ብትባሉ መልሳችሁ ምንድነው?

ገብሩ አስራትና ገብረ አበሮች በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ለአስራ ሰባት አመታትት ያፈሰሳችሁት ደም የገደላችሁት ህዝብ ምንም ስሜት ስለአልሰጣችሁ ፣ለአስራ ሰባት አመታትት በነጻነትና በደሞክራሲ ስም የህዝቡን ንብረትና ሀብት ዘርፋችሁት ለዛሬው ድህነትና ውድቀት ካደረሳችሁ በኋላ ዛሬ መድረክ ለኢትዮጵያ ደሞክራሲ በማለት አዲስ አመራር ልታስተርምሩን ተነስታችኋል፣ ባለፉት ሰላሳ አመታት ለሰራችሁት ግፍና በደል መታሰር ሲገባችሁ፣ እንደ ጲላጦስ በደም የተጨማለቀውን አጅችሁን አጥባችሁ አለቃችሁን መሪያችሁን መለስ ዜናዊን ለመክሰስ የእኛን ትብበር ትፈልጋላችሁ፣ የእኛን ትበበር የፈለጋችሁት የሰራችሁትን ግፍና በደል በመዘንጋት ሳይሆን እኛን ኢትዮጵያውያንን ምንም የማናውቅ ፈሪዎች ሆዳሞች ስልሆኑ ይከተሉናል በማለት ነው፣ ለዚህም አንድ ማስረጃ አናቅርብ፣ ብ 1983 ኢትዮጵያን በመሳሪያ ሀይል በሻቢያ ትብብር ከወረራችሁ በኋላ እኛ ተባብረን እንዳንነሳ ሁሉም በጎሳው ይደራጅ በማለት ለብዙ ሺህ አመታትት የነበርንን አንድነት በታትናችሁ በጎሳና በዘር ላይ የተመሰረተ አመራር ስላመጣችሁ ፣ተጋብተው ተዋልደው የልጅ ልጅ

ያሳደጊ በልና ሚስት በአንድ ቀን ጀምበር ተለያይተው ልጆቻቸውን እንደ በት እቃ ተከፋፍለው ሲለያዩ ለአስራ ሰባት አመታት ወላጆችና ልጆች በጎሪጥ ይተያያሉ፣ ይህ ተንኮል ከተሳካላችሁ በኋላ፣ በገሳ የተደራጁት ዜጎች የወያነ ድርጅት ተለጣፊ አባላት እንዲሆኑ በጥቅም በሹመት በማባበል በቁጥጥራችሁ ስር እንዲሆኑ ስለተገደዱ፣ በክልላችው ያለውን ሀብት በሙሉ ለትግራይ ማልሚያ እንዲያገቡ ስለታዘዙ፣ የአገረው ህዝብ በአገሩ ባይተዋር የበላተኛ ተመልካች እንዲሆን ስለተገደደ፣ አሁን የደረሰበትን ረሀብ ለመቋቋም ስለአልቻለ፣ እናትና ልጅ በየአለቱ ግባ መሬት ይባላሉ፣

አቶ ገብሩ ነሃሴ 20 2008 ባደረጉት ንግግር ስለመለስ ዘናዊ ተንኮልና አንባ ገነናዊነት በሰፊው ሲናገሩ ከዘህ በፊት እንደአልሰሙ እንደማያውቁ ይመስላል፣ እንዲህ የሚዋሹት እኛን ኢትዮጵያዊያኖችን ለማታለል ነው ይህ ውሸት እኛን አታለው የስልጣን እርካብ አድርገው በአዲስ ዘደ ስልጣን ለመያዝ ነው፣ አቶ ገብሩ ያደረጉትን የስምንት ገጽ ነግግር በንገመግመው የመለስ ዘናዊን ወንጀል፣ ስህተት ተንኮልና ሴራ የሚያጋልጥ ብቻ ነው። አቶ ገብሩ የመለስን ወንጀል እያውቁ በምስጢር ይዘው ዛሬ የሚነግሩን እኛን አስፈራርተው ለሳቸው ጥቅም እንድንዋጋላችው የሚፈልጉ ከሆነ ለላ ሞኝ ሰው ይፈልጉ፣ አቶ ገብሩ በንግግራችው ስለአገር ሉኡላዊነት ደጋግመው ይናገራሉ፣ የዘፈን ዳር ዳሩ አስክስካ ነው እንደሚባለው፣ የሳችው ፍላጎት ለረጅም አመታት የትግራይን ክልል ከትዮጵያ ገንጥሎ እንደ ኤረትራ ነጻ ለመድረግ ነው፣ ባለፉት አስራ ሰባት አመታት ከመላ ኢትዮጵያ የሰበሰቡትን ሀብት ትግራይ ክልል ስለአዋሉት ክልሉ በፖለቲካ በኤኮኖሚ በማህበራዊ ኑሮ በጣም ስለለማ፣ የክልሉ ሉኡላዊነት ከሌላው የኢትዮጵያ ግዛቶች የተለየ በመሆኑ በልዩ ባጀት እንዲተዳደር ለማድረግ የተቀደ ዘደ ነው፣ የጦሩ ሀይል እግረኛውም ሆነ በራሪው ወደትግራይ ስልተወሰደ በአጅ አዙር በኢትዮጵያ ወጪ ለመኖር ይፈልጋሉ፣ ለአስራ ሰባት አመታት በእኛ ወጪ የኖሩት አንሶ አሁን ደግሞ እድሜ ልካቸውን ሊያልቡን ይፈልጋሉ፣ ለምን? እነሱ የኢትዮጵያ ዘበኩር ልጆች ናቸው? ይህ የመገንጠል አቅድ የመለስ ቢሆንም፣ መለስ ይህንን ካደረገ ገብሩ አስራትና ሰዬ አብርሃ ስለሚባራሩ ሳይቀድማቸው ሊቀድሙት ይፈልጋሉ፡ ሁለቱ ወያነዎች መለስን በጣም ስለሚጠሉ አሱን ለማስወገድ የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም፣ አቅዳቸው መለስን አብረው ሰዬ አብርሃን ለመተካት ስለሆነ በሰሞኑ ወደ እኛ የቀረቡን በእኛ መስዋእትነት መለስን ለመቅበር ስለሆነ በዝምታ ከማየት በስተቀር ለእነሱ ጥቅም አንዲት ጠብታ ደም ማፍሰሰ አይገባንም።የመለስ የገብሩ የሰዬ ፍላጎት ትግራየን ከኢትዮጵያ ለመገንጠል ስልሆነ መንገዱን ጨርቅ ያድርግላቸው፣ የትግራይ ህዝብ ስጋችን አካላችን ስልሆነ በጋራ ትግል የጋራ ጠላቶቻቸንን እናስ ወግዳለን።፡ከዘህ ጽሁፍ ጋር የተያያዘው አባሪ ፎቶ አንደኛው የጸጋዬ ገብረ መድህን ደብተራው ሲሆን ገዳዩ ዛሬም በመካከላችን ይገኛል።

ፍራንክፉርት ጥቅምት 22/2001        02.10.3008